# በኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 1106/2017 ማብራሪያ

## መግቢያ

በቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1051/2009 ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 433/2011 አንቀፅ 15 ሥር እንደተደነገገው በቡና ላኪነት ሥራ ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊኖረው እንደሚገባ ተገልጸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን በሕግ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባር መካከል ሕጎችን፣ደንቦችንና መመሪያዎችን በማዘጋጀት በሚኒስቴሩ ይሁንታ ሲያገኝ ለመንግሥት አቅርቦ እንደሚያጸድቅ በባለሥልጣኑ መቋቋሚያ ደንብ ቁ.364/2008 አንቀጽ 6 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ቀደም ተዘጋጅቶ ሲሠራበት ያለው የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር መመሪያ ቁ.1100/2017 ስለ የቡና ለኪ የብቃት ማረጋገጫ ምሳክር ወረቀት አሰጣትና እድሳት አስመልክተው የተደነገጉ ድንጋጌዎች በሥራ አፈጻጸም ወቅት ክፍተት የታየበት በመሆኑ አሁን እየጨመረ የመጣውን የቡና ኤክስፖርት መጠንና የብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ ማስተናገድ፣ክትትና ቁጥጥር ማድረግ ላይ ሕገ-ወጥ የቡና ንግድ (ኮንትሮባንድ)፣ ሓሰተኛ የቡና ንግድማስረጃዎን (የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት) አመሳስሎ ማዘጋጀት፣ የኤክስፖርት ዳረጃ ያለውን ቡና በመሠወር በአገር ውስጥ በሕገወጥ መንገድ መሸጥ፣ ወዘተ ችግሮች ከጊዜ ወደ ጊዚ እየጨመረ በመምጣቱ አገራችን ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሬ እንዳታገኝ አሉታዊ ተጥዕኖ እየፈጠረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑማ በተቋማችን ለሚሰራው የድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ተግባር ላይ ጫና ከመፍጠሩም በላይ ለህገ-ወጥ የቡና ንግድ፣ ለጥራት መጓደል፣ ላልተገባ ሀገር ውስጥ ዋጋ ጭማሪ፣ በምርት ግዥ ወቅት ያልተገባ የምርት ሽሚያ እና ክምችት ህግና ስርአትን አክብረው በሚሰሩ ላኪዎች ላይ የምርት እጥረት በመፍጠር አለማቀፍ ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደር በሀገራችን ዘላቂ ጥቅም ላይ ስጋት እንዲፈጠር ማድረጉ በጥናት ተረጋግጧል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል የቡና ላኪዎች የላኪነት የምስክር ወረቀቱ ከተሰጣቸው በኋላ ወደ ተግባር የማይገቡ ወይም በበቂ ሁኔታ ቡናውን ወደ ውጭ የማይልኩ ወይም ቡናውን ከገዙ በኋላ ወደ ውጭ ሳይልኩ በሕገ-ወጥ መንገድ ግብይት በሚፈጽሙና በየአመቱ እድሳት እንዲደረግላቸውና አዲስ ወደ ዘርፉ ለመቀላቀል በሚጠይቁት አመልካቾች ላይ ውጤታማ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ጠንካራ የሕግ ሥርዓት እንዲኖር

መመሪያውን ማሻሻል በማስፈለጉ የቀረበው ማሻሻ መመሪያ ቁጥር---/2017 ማብራሪያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በዚሁ መሠረት በቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 1100/2017 ከተደነገጉት ድንጋጌዎች መካከል እንዲሻሻል የተደረጉት በክፍል አምስት ሥር ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣እዲሳት፣ዕገዳና ስረዛ የተደነጋጉት ድንጋጌዎች ሲሆን የማሻሻያ መመሪያው በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፋፍሎ 12 ንዑሳን ቁጥሮችና የተለያዩ የንዑስ ንዑሳን ድንጋጌዎችን በመያዝ የተዘጋጀ መቡኑን በዚህ የማሻሻያ መመሪያ መብራሪያው እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

- **ዓላማ**
  - የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አገልግሎት አሰጣጥን ግልፅ፣ ቀልጣፋ፣ወጪ ቆጣቢና ዘመናዊና ወቅታዊ ማድረግ፣
  - የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አገልግሎት አሰጣጥ ሥዓትን በማሻሻል፣በብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ በእድሳትና ስረዛ ሥራ ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን ለማስወገድ፣
  - በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ጥራቱን የጠበቀ ቡና ለውጭ ገበያ በመላክ ሀገራችን ከዘርፉ የሚታገኘውን የውጭ ምንዛሬ እንዲጨመርና ቀጣይነት ያለው ተጠቃሚነት በዘላቂነት እንዲቀጥል ማድረግ፣
  - የቡና ልማትና ግብይት ተዋንያን በቡና ላኪነት ሥራ ላይ ፍትሃዊና ተወዳዳሪ በሆነ መንገድ በመሣተፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
  - የምስክር ወረቀቱ ከተሰጣቸው በኋላ ወደ ተግባር የማይገቡ፣በበቂ ሁኔታ ቡናውን ወደ ውጭ የማይልኩ፣ በሕገ-ወጥ መንገድ ግብይት በመፈጸም በየዓመቱ እድሳት እንዲደረግላቸውና አዲስ ወደ ዘርፉ ለመቀላቀል በሚጠይቁት አመልካቾች ላይ ውጤታማ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት የሕግ ሥርዓት መዘርጋት፣
- **የመመሪያው አስፈላጊነት**

  በመመሪያ ቁጥር 1100/2017 ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አገልግሎት አሰጣጥ፣ እድሳትና ስረዛ የተደነገጉ አንዳንድ ድንጋጌዎች አሁን ባለው የቡና ግብይት ሥራ ጋር ባለመጣጣማቸው ለህገ ወጥ የቡና ንግድ መስፋፋት፣ ለቡና ጥራት መጓደል፣ ላልተገባ ሀገር ውስጥ ዋጋ ጭማሪ፣ በምርት ግዥ ወቅት ያልተገባ የምርት ሽሚያና ክምችት ችግሮች እየተበራከቱ በመምጣታቸው በግብይት ሥራው

ክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር ሥርዓት ላይ ክፍተት በመፈጠሩ፣ ህግና ስርዓትን አክብረው በሚሰሩ ላኪዎች ላይ የምርት እጥረት በመፍጠር ዓለም ዓቀፍ ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደሩና በሀገራችን ዘላቂ ጥቅም ላይ ስጋት እየሆነ በመምጣቱ ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣ እዲሳት፣ ዕገዳና ስረዛ የተደነገጉትን አንዳንድ ድንጋጌዎችን ማሻሻል አስፈልጓል ፡፡

በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ ቡና እና ሻይ ባለሥልጣን በቡና ብቃት የምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣እዲሳና እገዳ አፈጻጸም ወቅት የታዩትን ችግሮች ለመፍታት ጥናት እንዲካሄድ የጥናት ቡድን አቋቁሞ በማሰማራት የዳሳሳ ጥናት ተሠርቶ የቀረበ ሲሆን በጥናቱ ግኝት ውጤት የተለዩ ክፍተቶችና የተሰጡ የመፍትሔ አስተያየቶችን መነሻ በማድረግ ፌዴራል አስተዳደር ሥነሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 እና የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይህ ማሻሻያ ረቂቅ ተዘጋጅቷል፡፡

1.የተሻሻሉና አዲስ የተካተቱ ድንጋጌዎች ማብራሪያ

1/ በመመሪያው ክፍል 2 ተራ ቁጥር 2.5 ንኡስ ቁጥር 1 ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተዘረዘሩት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሐ) ተጨምሯል፡፡

- በስራ ላይ ያለው የመመሪያው የቢሮና የሰው ሀይል አደረጃጀት መስፈርት ላይ ስለቡና ጥራት መመርመሪያ ላቦራቶሪ የሚያነሳው ነገር ባለመኖሩ ይህ ደግሞ አሁን ላይ ዘርፉ በዓለም አቀፍ ደረጃ መስፈርት በመሆኑና ተወዳደሪ እንዲሆን በማስፈለጉ ማሻሻያው ላይ የሚከተለው ፊደል ተራ (ሐ) በአዲስ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

ሐ) ማንኛዉም የውጪ ቡና ላኪ ከአርሶአደር ላኪ በስተቀር ቢያንስ መሰረታዊ የቡና ጥራት ምርመራ ሊያከናውን የሚችልበት በባለስልጣኑ ብቃቱ የተረጋገጠ የቡና ላቦራቶሪ ሊኖረው ይገባል፣

2/ የመመሪያው ክፍል 2 ተራ ቁጥር 2.5 ንዑስ ቁጥር (2) ፊደል ተራ (ሐ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

- በስራ ላይ ያለው መመሪያ ክፍል 2 ተራ ቁጥር 2.5 ንኡስ ቁጥር (2) ፊደል ተራ (ሐ) ላይ ስለ ቡና ጥራት ምርመራ ባለሙያ ዝቅተኛ መስፈርት ምን እንደሆነ የማይገልጽ በመሆኑና እና አንድ ባለሙያ ለምን

ያህል ላኪዎች ማገልገል እንደሚችል የሚወስን ባለመሆኑ እንዲሁም ቡና ጥራት ምርመራ ባለሙያ በሙያው ሁለት አመት ያገለገለ የሚለው በሙያው ሰልጥነው ልምድ የሌላቸውን አዳዲስ ጀማሪ ባለሙያዎችን ስለሚገድብ ማካተት በሚያስችል መልኩ እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

"ሐ) የቡና ጥራት ባለሙያ ሆኖ የሚቀጠር ሰዉ ዕድሜው ከ18 ዓመትና በላይ የሆነ፣ በትምህርት ዘግጅቱ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው፣ ዕውቅና ካለው የቡና ማሰልጠኛ ተቋም የታደሰ የቀማሽነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያለውና በሙያው ከ0 ዓመት አገልግሎት ያለው ሆኖ አንድ የቡና ጥራት መርማሪ ለአንድ የቡና ላኪ ብቻ ያገለግላል፤"

3/ የመመሪያው ክፍል 5 ተራ ቁጥር 5.1 ንዑስ ቁጥር (1) እና (2) ተሰርዘው የሚከተሉት ንዑስ ቁጥሮች "(1)" እና "(2)" ተተክተዋል፡፡

- በስራ ላይ ያለው የመመሪያው ክፍል 5 ተራ ቁጥር 5.1 ንዑስ ቁጥር (1) ለሰው ንክኪ የተጋለጠ፣ በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ፣ ለብልሹ አሰራርና ቅሬታ ተጋላጭ በመሆኑ እነዚህን ክፍተቶች ለማስወገድ በቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ አገልግሎት አሰጣጥን እንዲኖር ታስቦ ተተክቷል፡፡

    3.1 የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አገልግሎት ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ማመልከቻውን እና በመመሪያው አዝል 1 ላይ የተመለከተውን ቅፅ ሞልቶ እንዲሁም በደንቡና በዚህ መመሪያ የተገለፁትን መስፈርቶች ስለማሟላቱ የሚያሳዩ ማስረጃዎችን ስካን አድርጎ ለባለስልጣኑ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ማቅረብ አለበት፤

- በስራ ላይ ያለው የመመሪያው ክፍል 5 ተራ ቁጥር 5.1 ንዑስ ቁጥር (2) ለሰው ንክኪ የተጋለጠ፣ በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ፣ ለብልሹ አሰራርና ቅሬታ የተጋለጠ አገልግሎት አሰጣጥ በመሆኑ እነዚህን ለማስወገድ በቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ ዘመናዊ፣ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ አገልግሎትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የተተካ ቢሆንም በሲስተም መቋረጥ ወይም ተደራሽነት ምክንያት በቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ የሚሰጠው አገልግሎት ቢስተጓጎል መጉላላትን ለማስቀራትና የቅሬታ ምንጭ እንዳይሆን በአካል በመቅረብ አገልግሎቱ የሚገኝበት አማራጭ እንዲኖር ተደርጎ ተተክቷል፡፡

3.2) በዚህ ክፍል ንኡስ ቁጥር (1) ላይ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በሲስተም መቋረጥ ወይም ተደራሽነት ምክንያት በኤሌክትሮኒክስ

ዘዴ ማቅረብ የማይቻልበት የተረጋገጠ ሁኔታ ሲያጋጥም በአካል ማቅረብ ይችላል፤

4/ በዚሁ የመመሪያው ክፍል 5 ተራ ቁጥር 5.1 ንዑስ ተራ ቁጥር (7) በሚከተለው ንኡስ ቁጥር “(7)” ተሻሽሏል፡፡

1) በስራ ላይ ያለው የመመሪያው ክፍል 5 ተራ ቁጥር 5.1 ንኡስ ቁጥር 7 የቅሬታ አቀራረብን በተመለከተ በአካል ብቻ ቅሬታቸውን ማቅረብ እንዳለባቸው ከተደነገገው በተጨማሪ በቴክኖሎጂ በታገዘ፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ እንዲያቀርቡ ሆኖ ተሻሽሏል፡፡

7) የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አገልግሎት ማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም አመልካች በብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው ክፍል የተሰጠውን ውሳኔ የሚቃወም ከሆነ ቅሬታውን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ወይም የኤልክትሮንክ አገልግሎት በማይኖርበት ጊዜ በአካል በፅሁፍ ለባለስልጣኑ በ5 የስራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላል፣

5/ የመመሪያው ክፍል 5 ተራ ቁጥር 5.2.6 ንኡስ ተራ ቁጥር (2) በሚከተለው ንኡስ ተራ ቁጥር “(2)” ተሻሽሏል፡፡

- በስራ ላይ ያለው የመመሪያው ክፍል 5 ተራ ቁጥር 5.2.6 ንኡስ ተራ ቁጥር (2) ለግል አመልካች አስቀምጦት የነበረው የመነሻ ካፒታል አሁን ካለው ወቅታዊና የአለም የቡና ገበያ ዋጋ ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ ብዛት ያላቸው ሰዎች የላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወራት አውጥቶ ቡና ገዝቶ ወደ ውጪ ሳይልኩ በሀገር ውስጥ በሕገ-ወጥ መንገድ የሚሸጡ እተበራከቱ በመምጣቱ በሕጋዊ ነጋዴዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕና ከማሳደሩም በላይ አገራችን ከቡና የሚታገኘውን የውጭ ምንዛሬ እንዳታገኝ እደረገ በመሆኑ ችግሮቹን በማከላከልየሚረዳና ሊያሰራ የሚያስችል የቡና ላኪነት መነሻ ካፒታል መጠን ኖሮት ባለስልጣኑ የሚያወጣውን ወቅታዊ የቡና መግዣ ዋጋ መሠረት ባደረገ መልኩ እንዲስተካከል ተደርጎ ተሻሽሏል፡፡

2) የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚጠይቀዉ የግል አመልካች ከሆነ ለሥራው የሚያስፈልግ መነሻ ካፒታል ቢያንስ 15,000,000.00 (አስራ አምስት ሚሊዮን) ብር እና የአንድ ዓመት የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚያሳይ በባንክ የተረጋገጠ የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፤

6/ የመመሪያው ክፍል 5 ተራ ቁጥር 5.2.6 ንኡስ ተራ ቁጥር (3) በሚከተው ንኡስ ተራ ቁጥር "(3)" ተሻሽሏል፡፡

- በስራ ላይ ያለው የመመሪያው ክፍል 5 ተራ ቁጥር 5.2.6 ንኡስ ተራ ቁጥር (3) ለአክሲዮን ማህበር ወይም ኃላፊነቱ ለተወሰነ የግል ማህበራት አመልካቾች ሌሎችንም የንግድ ድርጅቶችን እንዲያካትት የተደረገ መሆኑና አስቀምጦት የነበረው የመነሻ ካፒታል ለግል አመልካች ተገለጸው ጋር በተመሳሳይ አሁን ካለው ወቅታዊ የቡና መግዣ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ በመሆኑ ሊያሰራ በሚችል የካፒታል መጠን ወቅታዊ የባለስልጣኑን የቡና መግዣ ዋጋ ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንዲስተካከል ተደርጎ ተሻሽሏል፡፡
- የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚጠይቀዉ የንግድ ማህበር ከሆነ የመነሻ ካፒታል 20,000,000.00 (ሃያ ሚሊዮን) ብር በባንክ የተረጋገጠ ማስረጃ እና ከባለአክሲዮኖቹ ቢያንስ ሁለት ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸው አባላት የአንድ አመት የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚያሳይ በባንክ የተረጋገጠ የሰነድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤

7/ በመመሪያው ክፍል 5 ቁጥር 5.1 ንኡስ ቁጥር ከ1-9 የተዘረዘሩት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት አዲስ ንኡስ ቁጥር 10፣ 11 እና 12 ተጨምሯል፡፡

- በስራ ላይ ያለው በመመሪያው ክፍል 5 ቁጥር 5.1 ንኡስ ቁጥር ከ1-9 የተዘረዘሩት እንደተጠበቀ ሆኖ ንኡስ ቁጥር 10 የተጨመረበት ምክንያት አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የተፈቀደለት ግለሰብ ላኪ በአካል በመቅረብ ወይም በህጋዊ ተወካዩ አማካኝነት ቀርቦ ፊርሞ እንዲወስድ የሚገደድ ሲሆን ይህም አሰራር ጉዳዩ በቀጥታ የማይመለከታቸው ጉዳይ አስፈጻሚ በመምሰል በግብይት ሥርዓቱ

ላይ ችግር እየፈጠሩ ያሉ ህገ ወጥ ደላላዎችን ለመከላከል ታስቦ የተጨመረ ነው፡፡

- 10) ተፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የተፈቀደለት ላኪ በአካል በመቅረብ ፈርሞ መውሰድ አለበት፤
- በዚሁ መመሪያው ክፍል 5 ቁጥር 5.1 ንኡስ ቁጥር ከ1-9 የተዘረዘሩት እንደተጠበቀ ሆኖ ንኡስ ቁጥር 11 የተጨመረበት ምክንያት አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የተፈቀደለት የንግድ ድርጅት ወይም ላኪ ድርጅት የማሕበሩ ሊቀ መንበር ወይም የማህበሩ ህጋዊ ሥራ አስክያጅ ቀርቦ ፈርሞ እንዲወስድ የሚገደድ ሲሆን ይህም አሰራር ጉዳዩ በቀጥታ የማይመለከታቸውን በግብይት ሥርዓቱ ላይ ችግር እየፈጠሩ ያሉ ህገ ወጥ ጉዳይ አስፈፃሚዎችና ደላላዎችን ለመከላከል ታስቦ የተጨመረ ነው፡፡

11) አመልካቹ የንግድ ማህበር በሆነ ጊዜ ሥራ አስኪያጅ በአካል ቀርቦ ፈርሞ መዉሰድ ይኖርበታል፤

የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የተፈቀደለት ላኪ ወይም የሕብረት ሽርክና ማሕበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር ወይም የአክስዮን ማህበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሊቀ መንበር ወይም የማህበሩ ህጋዊ ሥራ አስክያጅ በአካል ጉዳተኝነት፣ ታሞ ሀኪም ቤት በመተኛት፣በሕመም የአልጋ ቁራኛ በመሆን፣በፍርድ ቤት ተወስኖበት በማረሚያ ወይም ሕጋዊ መቆያ ቦታ በመሆን፣ በውጭ ሀገር በመኖር እና ሌሎች ከአቅም በላይ በሆኑ ምክኒያቶች በአካል ቀርቦ ፈርሞ መቀበል ካልቻለ በልዩ ሁኔታ በሕጋዊ ተወካያቸው ቀርቦ ፈርሞ መውሰድ እንደምችሉ በመመሪያው እንዲካተት ተደረጓል፤

10) በንዑስ ቁጥር (11) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ አስኪያጁ በመታሰሩ፣ በህመም፣ ከሀገር ዉጭ በመሆን እና ሌሎች ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች በአካል ቀርበው ፈርሞ መውሰድ የማይችል ሲሆን ሕጋዊ ተወካዩ በአካል ቀርበው ፈርሞ መውሰድ ይችላሉ፤

8/ የመመሪያው ክፍል 5 ተራ ቁጥር 5.2 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

- በስራ ላይ ያለው መመሪያ ክፍል 5 ተራ ቁጥር 5.2 ላይ ያለው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሀሰት የሰነድ ማጭበርበር የተጋለጠ በመሆኑ ሚስጥራዊነቱን ማስጠበቅ የሚችል መለያ እንዲኖረው ተደርጎ ተሻሽሏል፡፡

5.2) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ:-

መስፈርቶች በሚሟላት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለሚጠይቁ ላኪዎች ባለሥልጣኑ በቀላሉ ለብልሽት የማይጋለጥ ባለቀለም ሚስጥራዊ መለያ ኪው አር ኮድ በማዘጋጀት ይሰጣል፤

9/ የመመሪያው ክፍል 5 ቁጥር 5.3 ንኡስ ቁጥር (7) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ ቁጥር (8) ተጨምሮ ንኡስ ቁጥር (8) እና (9) የነበረው ንኡስ ቁጥር (9) እና (10) ሆኖ ተሸጋሽገዋል፡፡

- በስራ ላይ ያለው የመመሪያው ክፍል 5 ቁጥር 5.3 ንኡስ ቁጥር (6) እና (7) ላይ የተደነገጉት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እድሳትን በተመለከተ አሳማኝ ምክንያት የሚለው ግልፅነት የሚጎድለው፣ ለትርጉም ተጋላጭና ለብልሹ አሰራርም በር የሚከፍት በመሆኑ ተሰርዞ ከታች ባሉት ንኡስ ቁጥሮች ተተክቷል፤

  "8) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የወሰደ ቡና ላኪ ከአርሶ አደር ላኪ በስተቀር በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ወደ ቡና መላክ ስራ መግባት አለበት፣ እንዲሁም የእድሳት ወቅቱን ጠብቆ ማደስ አለበት፤"

በስራ ላይ ያለው የመመሪያው ክፍል 5 ቁጥር 5.5 ንኡስ ቁጥር (1) ላይ (ሀ) እና (ለ) የተዘረዘሩት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ ሐ የተጨመረው የእድሳት ወቅቱን እስከ 3 ወር ጠብቀው ያላደሱ ጉድለቱ እስክስተካከል ድረስ ታግዶ ለተወሰነ ጊዜ ከቆየ በኋላ ምን ይሆናሉ የሚለውን ለመመለስ የተካተተ ድንጋጌ ነው፡፡

"ሐ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠዉ ሰዉ የፈጸመዉ ጉድለትን እንዲያስተካክል በባለስልጣኑ የብቀት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የታገደ እንደሆነ እገዳዉ ከተጣለበት ቀን አንስቶ ባሉት ሶስት(3) ወር ዉስጥ ተገቢ ማስተካከያ አድርጎ ያላሳደሰ እንደሆነ የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል፤"

11/ በመመሪያው ክፍል 14 ቁጥር 14.1 ንኡስ ቁጥር ከ1-18 የተዘረዘሩት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለው አዲስ ንዑስ ቁጥር 19 ተጨምሯል፡፡

- በመመሪያው ክፍል 14 ቁጥር 14.1 ንኡስ ቁጥር ከ1-18 የተዘረዘሩት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለው አዲስ ንኡስ ቁጥር 19 እንዲጨመር የተደረገው የግብይት ሰንሰለቱን እንዳያዛባ፣ ማጭበርበርን ለመከላከል፣ የግብይት ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥና የህገ ወጥ ንግድን ለመከላከል እንዲረዳ ታስቦ የተጨመረ ድንጋጌ ነው፡፡

    19) በቡና ላኪነት ሥራ የተሠማራ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት የቡና አቅራቢ ላኪ ወይም አልሚ ላኪ ወይም የኮሜርሻል ላኪ በአንድ ስም ከአንድ ዓይነት የላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በላይ ማውጣት አይችልም፡፡

## <u>የባለድርሻ አካላት መድረክ በማዘጋጀት እንዲሳተፉ ማድረግ፡-</u>

ረቂቅ መመሪያው ከተዘገጀ በኋለ በአዋጅ ቁጥተር1183/2012 ባለድርሻ አካላት ግብዓት እንዲሰጡበት ለማድረግ አስተያየት መስጫ መዝገብ ተዘጋጅቶ በአከል በመቅረብ ወይም በኢ-ሜል፣ በቶቴሌግራም፣በዋትስ-አፕ፣በባለሥልጣኑ ድህረ-ገጽ፣ በሚዲያና በጋዜጣ ተላልፈዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ግንቦት 3 ቀን 2017 ዓ/ም በባለሥልጣኑ ድህረ-ገጽ የተለቀቀ ሲሆን፣ በኢ ቢ ኤስ ሚዲያ፣ አዲስ-አድማስ ሚዲያ፣ በሁሌ-አዲስ ሚዲያ፣ በብስራት ኤፍ አም አየር ላይ ውሏል፡፡ እንዲሁም ከግንቦት 7 ቀን 2017 ዓ/ም ጀምሮ ማንኛውም አስተያየት ለመስጠት የሚሰልግ ሰው በአክል ወይም ኢ-ሜይል ወይም በቴሌግራም አድራሻችን በመጠቀም አስተያየቱን እንዲሰጥ ለ15 ቀናት አየር ላይ እንዲቆይ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞወጥቷል፣ እንዲሁም በሪፖርተር ጋዜጣም በዝርዝር ተዘግቧል፡፡ ረቂቅ መመሪየው በኦን-ላይን ለበላይ አመራሮች ቀርቦ አስተያየት የሰጡበት ሲሆን በተጨማሪም ግንቦት 11 ቀን 2017 ዓ/ም ለአጠቃላይ የባለሥልጣኑ ማናጅሜንት አባላት ቀርቦ አስተያየትና ግበዓት ተሰጥቶበታል፡፡ እንዲሁም ግንቦት 15 ቀን 2017 ዓ/ም የቡና ላኪዎች እና የቡና ላኪ ማህበራት መድረክ በማዘጋጀት ወይይት ተደርጓል፡፡

ከተሳታፊዎች የቀረቡ አስተያየት በተወሰነ ደረጃ በግብዓትነት የተወሰዱ ቢሆንም በአብዛኛው ግን ማብራሪያ ተሰጥቶበት በቀረቡ ጉዳዮች ላይ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

በአጠቃላይ በሁሉም መድረኮች የተነሱ ጥያቄዎች፣አስተያየቶች ወይም ግብዓቶችና በባለሥልጠኑ የበላይ አመራሮች የተሰጡ መብራሪያና ምላሽ ተያይዞ ቀርበዋል፡፡

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን

አዲስ አበባ

ሐምሌ ---- ቀን 2017